# የንብረት ማስመለስ አዋጅ አጭር ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

ወንጀል ለተለያየ ዓዓላማ ሊፈጸም የሚችል ቢሆንም ገንዘብ የሚያስገኙ ወንጀሎች የሚፈጸሙት ፈፃሚዎቹ በዋናነት ከወንጀል ድርጊታቸው የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት በማሰብ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ከሚፈጸሙ ወንጀሎች መካከል የሙስና ወንጀሎች በተለይም ጉቦ መቀበል ፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ሕገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር፥ የተከለከሉ ዕፆችን ማዘዋወር፣ የሃሰት ገንዘብ ማተም፣ ሕገ ወጥ ሀዋላ፣ የታክስ እና የኮንትሮባንድ ወንጀሎችን ማንሳት ይቻላል፡፡ እነዚህን መሰል ወንጀሎች በባህሪያቸው ለወንጀል ፈጻሚዎች ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገኙ ሲሆኑ በሀገርማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ የሚያሳርፉት አሉታዊ ተጽዕኖ ደግሞ በተቃራኒው እጅግ አደገኛና ውስብስብ ነው፡፡

በዚህም ምክንያት ወንጀልን ከመከላከል እና አጥፊዎች ላይ አስተማሪ የሆነ ቅጣት ከማስተላለፍ አንፃር በወንጀሉ የተሳተፉ ሰዎችን በወንጀል ተጠያቂ ከማድረግ በተጨማሪ የወንጀል ፍሬ ወይም ለወንጀል መፈጸሚያነት የዋለውን ንብረት መውረስ ተገቢ ነው፡፡ በወንጀል የተገኘ ሃብትን የማስመለስ ሂደት የተለያዩ ደረጃዎችን የሚያልፍ ሲሆን በዚህም የወንጀል ምርመራን መሰረት በማድረግ (በመርህ ደረጃ የወንጀል ምርመራ እንደተጀመረ እና በልዩ ሁኔታ የወንጀል ምርመራ ከመጀመሩ በፊት) የንብረት መለየት፣ የንብረት እግድ፣ ንብረት መያዝ እና በአስተዳደር ስር እንዲቆይ ማድረግ እንዲሁም የንብረት ውርስ ተግባራት ዋነኛዎቹ እንደሆኑ ይታመናል፡፡

ለዚህም አፈጻጸም ወጥና ራሱን የቻለ የንብረት ማስመለስና አስተዳደር ሕግ ሊኖር ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ራሱን የቻለ በወንጀል የተገኘ ሃብትን የሚመለከት ሕግ ባይኖራትም በተለያዩ አዋጆች ስር በወንጀል የተገኘ ሃብትን ስለማስመለስ በተመለከተ ተፈጻሚነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ተካተው እናገኛለን፡፡ ሕግ በነዚህ አዋጆች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የንብረት ማስመለስ ድንጋጌዎችም ተበታትነው ከመገኘታቸው ባሻገር ተፈፃሚነታቸውም በአዋጆቹ ስር ለተደነገጉት የወንጀል አይነቶች ብቻ እንደመሆኑ መጠን ወጥ የሆነ የንብረት ማስመለስ እና ማስተዳደር ሕግ አለመኖሩ በአዋጆቹ ባልተካተቱ እና ከፍተኛ የሆነ የንብረት ጥቅም ወይም ጉዳት በሚያስከትሉ

የወንጀል አይነቶች የንብረት ማስመለስ ሂደት መሰረታዊ የሆነ የሕግ እና አፈፃፀም ክፍተት እንዲኖር አድርጓል።

በመሆኑም እነዚህን በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተበታትነው ያሉትን የንብረት ማስመለስ እና አስተዳደር ድንጋጌዎች በአንድ ወጥ ሕግ ውስጥ በማካተት ለአፈጻጸም ምቹ የሆነ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሁኔታ በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ መርሆዎች መካከል አንዱ የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችንና ገንዘቦችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመያዝ፣ ለማገድ፣ ለመውረስ ወይም ለማስተዳደር የሚያስችል ግልጽና ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንደሚሆን እንዲሁም በዚሁ ፖሊሲ ተራ ቁጥር 3.16.3 ላይ ስለንብረት ማገድና መውረስ የተካተተ በመሆኑ በዚህ የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት አንድ ወጥ የሆነ ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ አዋጅ የተዘጋጀ ሲሆን፥ የአዋጁ ዝርዝር ማብራሪያ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

## 2. የአዋጁ አስፈላጊነት

የዚህ አዋጅ ዋነኛ ዓላማ የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችንና ገንዘቦችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመያዝ፣ ለማገድ፣ ለመውረስ ወይም ለማስተዳደር የሚያስችል ግልጽና ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ በማበጀት ማንም ሰው ከሕገ-ወጥ ድርጊት ማናቸውንም አይነት የኢኮኖሚ ጥቅም እንዳያገኝ ለማድረግ እና የንብረት ማስመለስ ሕግ ወንጀልን በመከላከል ሂደት ያለውን ከፍተኛ ሚና ለማሳካት የሚያስችል የንብረት ማስመለስና ማስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

ለዚህም ሲባል በአሁኑ ወቅት ከወንጀል ጋር ግንኙነት ያለውን ምንጩ ያልተወቀ ንብረትን ማስመለስ እንዲቻል እና በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተበታትነውና ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ሆነው ያሉትን የንብረት ማስመለስ እና መውረስ መሠረታዊ ድንጋጌዎች እና የሥነ-ሥርዓት ሂደቶች የንብረት ማስመለስና መውረስ ሂደት ውስጥ ያሉትን ልዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሁሉም አይነት ወንጀሎች የሚያገለግል አንድ ወጥ የሆነ ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ በማውጣት በንብረት ማስመለስና መውረስ ሂደት ውስጥም ሆነ ንብረቱ ከተወረሰ በኋላ የንብረቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስጠበቅ የመንግስትና የሃገሪቱን ጥቅም ማስከበር ነው፡፡

## 3. የአዋጁ አወቃቀር (አደረጃጀት)

አዋጁ ጠቅላላ ድንጋጌዎችንና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ጨምሮ በስምንት ክፍል እና በ 57 አንቀጾች የተዋቀረ ነው፡፡ ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ክፍል ሁለት ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን ማስመለስ፣ ክፍል ሶስት በንብረት ማስመለስ ሂደት ምርመራ የሚከናወንበትን ሁኔታ እና ሥነ-ሥርዓት እንዲይዝ ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡ ክፍል አራት ደግሞ ንብረት ስለማገድና ስለመያዝ ይደነግጋል፡፡ ክፍል አምስት ንብረት የመውረስ፣ ክፍል ስድስት ንብረትን ማስተዳደር ጉዳዮች እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በክፍል ሰባት ስለንብረት ማስመለስ ዓለም-አቀፍ ትብብር የሚደነግግ ሲሆን በመጨረሻም ክፍል ስምንት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን እንዲይዝ በማድረግ አዋጁ እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡

## 4. በአዋጁ የተካተቱ ዋና ዋና ድንጋጌዎች (የአዋጁ ይዘት)

በዚህ ንዑስ ክፍል በአዋጁ ውስጥ የተካተቱ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ዋና ዋና ድንጋጌዎች ቀርበዋል፡፡

### 4.1. የአዋጁን ስያሜ በተመለከተ

“የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንብረት ማስመለስ አዋጅ” የሚለው ስያሜ የተመረጠበት ምክንያት ወንጀል የሚለው ቃል ከገባ ሌሎች ንብረቶችንም፣ ወንጀልን ማቋቋም ሳይኖር የሚመለሱ፣ በወንጀል ሃላፊነት የማይረጋገጡ ንብረቶችንም የማያካትት በመሆኑ ሲሆን በተለይም ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን የማይሸፍን ስያሜ ይሆናል፡፡ የተለያዩ ሀገራትም በንብረት ማስመለስ ሕጎቻቸው ስያሜ “Asset Recovery Act” በሚል ሕጎቻቸውን የሚጠሩበት ሁኔታ አለ ከዚህ በተጨማሪም “ንብረት” መሆን አለበት በሚል የቀረቡት ሀሳብ በዋናነት በሕግ ሥርዓታችን ውስጥ እና በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የተለመደ የቃል አጠቃቀም በመሆኑ፣ ንብረት የሚለውን በትርጉም ክፍል በማስቀመጥ ቀላል የሆነ ትርጓሜ ያለው በመሆኑና ሊወረሱ የሚገቡ ሌሎች ነገሮችን ሊያጠቃልል የሚችል ቃል በመሆኑ “ሀብት” ከሚለው “ንብረት” የሚለው ቃል ተመርጧል፡፡

### 4.2. የተፈጻሚነት ወሰን

በጠቅላላ ድንጋጌዎች ውስጥ ከተካተቱ ድንጋጌዎች መካከል አንዱ በአንቀጽ 3 ስር የተካተተው የአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አዋጁ በማንኛውም

ሁኔታ ከወንጀል ድርጊት የተገኘን ንብረት ለማስመለስና ለመውረስ ዓላማ በሀገሪቱ ግዛት ውስጥም ሆነ ከአገሪቱ ግዛት ውጪ በተፈጸሙ ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ ይህም ሲባል ከአገር ውጪ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ ኢትዮጵያ ወንጀሉን የመክሰስ መብት ሲኖራትና የንብረት ማስመለስ እና መውረስ ሂደት ውስጥ የሚያልፉ ከሆነ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ እንደሚሆንባቸው ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት በሌላ አገር ውስጥ ክስ መመስረትን ሳይሆን በወንጀል ሕግ መሠረት ኢትዮጵያ ለንብረት ማስመለስ ሂደት ምክንያት የሆነውን ወንጀል የመክሰስ ሥልጣን በሚኖራት ጊዜ ንብረት ማስመለስን እና መውረስን የተመለከቱ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ የሚታዩ ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ማስመለስ ሂደትም በዚሁ አዋጅ እንደሚመራ በተፈፃሚነት ወሰን ስር በግልፅ ተደንግጓል፡፡

## 4.3. <u>የሕግ ሰውነት ያላቸው ተቋማት ተጠያቂነትን በተመለከተ</u>

] በወንጀል ሕጉ ላይ የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው አካላት በግልጽ የወንጀል ተጠያቂነት በሕግ ካልተቀመጠ ተጠያቂ የማይደረጉ ቢሆንም በንብረት ማስመለስና መውረስ ሂደት ውስጥ በግልጽ በሕግ ባይቀመጥም በአዋጁ መግቢያ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ማንኛውም ሰው ከወንጀል ድርጊት ጥቅም ማግኘት ስለሌለበት የወንጀል ተጠያቂነት ባይኖርም በወንጀል ድርጊት የተገኘውን ንብረት ከመውረስ የሚከለክል ሁኔታ ሊኖር ስለማይገባ በማንኛውም ሁኔታ የሕግ ሰውነት ያላቸው ተቋማት በወንጀል ድርጊት በመሳተፍ ያልተገባ የንብረት ጥቅም ማግኘታቸው ወይም ለሌላ ሰው ማስገኘታቸው ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ከተረጋገጠ በወንጀል የማይከሰሱ ቢሆንም ከድርጊቱ የተገኘ ንብረታቸው በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሠረተ ንብረት የመውረስ ሂደት ንብረታቸው እንደሚወረስ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በወንጀል ሕጉ መሠረት በጥፋተኝነት ላይ የተመሠረተ የንብረት መውረስ የሚደረግ ቢሆንም በወንጀል ሕጉ መሠረት በወንጀል ተከሰው ንብረታቸው የማይወረስ የሕግ ሰውነት ያላቸው ተቋማት በፈጸሙት ሕገ-ወጥ ድርጊት ጥቅም ካገኙ ወይም ለሌላ ሰው ካስገኙ ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰው ሲገኙ በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስ ክስ ሊቀርብባቸው የሚችልበት አዲስ ሥርዓት በዚህ አዋጅ ተዘርግቷል፡፡

## 4.4. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን ማስመለስ በተመለከተ

በአዋጁ አንቀጽ 5 ላይ አዋጁ ከመንግሥት እና ሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኞች ውጭ ባሉ ማኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን በማስቀመጥ በግሉ ዘርፍ ላይም ተጠያቂነት የሚያስከትል ሕግ መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህ አዋጅ ከተፈጥሮ ሰው በተጨማሪ የሕግ ሰውነት ባላቸው ድርጅቶች ላይም ተፈጻሚ እንደሚሆን ተካቷል፡፡

ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን በአንቀጽ 5 መንደርደሪያው ላይ "በሙስና ወንጀሎች አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ" የሚለው ሀረግ የተካተተው በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ውስጥ የመንግሥት እና የሕዝባዊ ድርጅቶች ሠራተኛ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ካለው በወንጀል የሚጠየቅ በመሆኑ ከእነዚህ ሰዎች ውጪ ያሉትን ብቻ በዚህ አዋጅ የሚሸፈኑና በወንጀል የማይጠየቁ መሆኑን በግልጽ መለየት በማስፈለጉ ነው፡፡ ይህም ሲባል ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ይገኛል ተብሎ የሚታሰበው የወንጀል ባህሪ ያለውን ድርጊት በመፈጸም ቢሆንም ተጠያቂነትን በተመለከተ በወንጀል ሳይሆን በፍትሐ-ብሔር ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጥ በማድረግ ምንጩ ያልታወቀው ንብረት የሚወረስበት አግባብበ አዋጁ ውስጥ ተቀምጧል፡፡

በዚህም መሠረት በዚህ አዋጅ ውስጥ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ለማስመለስ ከህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን ንብረት እንዳለው ለማስረዳት ምክንያታዊ የሆነ የወንጀል ጥርጣሬ በኖረ ጊዜ ብቻ ምንጩ ያልታወቀው ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንደሚወረስ ተደንግጓል፡፡ ይህም ሲባል ወንጀልን በምናስረዳበት የማስረጃ ምዘና ማስረዳት የሚጠይቅ ባይሆንም የተፈጸመውን ወንጀል በግልጽ የሚያሳይ ምክንያታዊ ጥርጣሬን ለፍርድ ቤት ማስረዳት ይጠበቃል፡፡ በሌላ አገላለጽ ምንጩ ያልታወቀውን ንብረት ለመጠየቅ ወንጀልን ለማስረዳት በምንጠቀመው የማስረጃ ደረጃ ማስረዳት ስለማይቻል ምክንያታዊ የሆነ የወንጀል ጥርጣሬ መኖርን እንደቅድመሁኔታ በማስቀመጥ ድንጋጌው ተቀርጿል፡፡

ለዚህም ድንጋጌ መነሻ የተደረገው በፍትሐ-ብሄር ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ማፍራትን ተጠያቂ ለማድረግ በወንጀል መጠርጠርን እንደ ቅድመ ሁኔታ ያደረጉ ሀገራትን ልምድ በመውሰድ ነው፡፡ ለዚህም እንደማሳያ የሚከተሉትን አገራት ልምድ ማየት ይቻላል፡፡ በአውስትራሊያ ኒው ሳውዝ ዌልስ ግዛት በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ አክት ላይ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት በፍትሐ-ብሔር ተጠያቂ ለማድረግ በቅድመ ሁኔታነት

ግለሰቡ በከባድ ወንጀሎች ጋር የተገናኘ እንደሆነ ወይም በማወቅም ይሁን ባለመወቅ ሌሎች ሰዎች በፈፀሙት ከባድ ወንጀሎች የተገኘ ሀብት ያገኘ እንደሆነ በዚህ ሕግ መሠረት ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ የአውስትራሊያ የኪውንስ ላንድ ግዛት እና የቪክቶሪያ ግዛቶች በሕጎቻቸው ላይ ግለሰቡ በከባድ ወንጀሎች ጋር የተገናኘ መሆን እንደሚገባው ያስቀምጣሉ፡፡

በሌላ በኩል የኬንያ የፀረ-ሙስና እና ኢኮኖሚ ወንጀሎች ሕግ ላይ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ተጠያቂ ለማድረግ በሙስና ወይም በኢኮኖሚ ወንጀሎች ጋር በተገናኘ ምክንያታዊ ጥርጣሬ መኖሩን ማስረዳት ይኖርበታል።

በተመሳሳይ የትሪንዳድ እና ቶቤጎ በሀብት ማስመለስ፣ማስተዳደር እና ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ሕግ ላይ በተመረጡ ወንጀሎች (specified offence) በምርመራ ወቅት መርማሪው የተጠርጣሪው ጠቅላላ ሀብት ከሕጋዊ ገቢው የበለጠ እንደሆነ ንብረቱ ከወንጀል ጋር የተገኘ እንደሆነ ምክንያተዊ ጥርጣሬ ካለው ጉዳዩ በፍትሐብሄር ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ምርመራ ለመጀመር መነሻ ሊሆን እንሚችል ያስቀምጣል።

ከላይ በተዘረዘሩት ሀገራት ልምድ ለማየት እንደሚቻለው ምንም እንኳ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ተጠያቂነቱ የፍትሐ-ብሔር ቢሆንም የምርመራውን መጀመር በዘፈቀደ እንዳይሆን በማሰብ ከወንጀል ድርጊት ጋር ግንኙነት ያላቸውን እና ለዚህም ምክንያታዊ ጥራጣሬ መኖሩን መርማሪው ወይም ክስ አቅራቢው ማስረዳት እንደሚኖርበት ደንግገው ይገኛሉ።

ሆኖም በአንቀጽ 5(2) ላይ የተካተተው ድንጋጌ ከወንጀል ድርጊት ጋር ግንኙነት መኖሩን በሚመለከት ምክንያታዊ ጥራጣሬ ባይኖርምሕጋዊ ገቢ እንዳለው የሚያስረዳ የተመዘገበበት ሥርአት እንደ ንግድ ፍቃድ፣ የስራ ቅጥር እና መሰል ሰነድ የሌለው ወይም ሕጋዊ ገቢያቸው አነስተኛ በመሆኑ ግብር ከመክፈል ነጻ የተደረጉ ሰዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያለው ንብረት ወይም የኑሮ ደረጃው ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ህጋዊ ገቢ የማይመጣጠን እንደሆነ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ባይኖርም የሚጠየቁበትን ልዩ ሁኔታ የሚያስቀምጥ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ይህም የተካተተበት ዋነኛ ምክንያት በአገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች ንብረታቸውን በቤት ሠራተኞቻው፣ በጥበቃቸው ወይም ምንም ዓይነት ገቢ በሌለው ግለሰብ ስም የሚያስቀምጡበት ሁኔታ ስላለ የእነዚህን ሰዎች ንብረት ምክንያታዊ ጥርጣሬን ሳናስረዳ ሕጋዊ ገቢያቸው ካላቸው ንብረት ጋር የማይመጣጠን መሆኑን በማስረዳት ብቻ ንብረቱ

የሚወረስበትን አግባብ ካላስቀመጥን ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን በአግባቡ ማስፈጸም ስለማይቻል ይህ ድንጋጌ በልዩ ሁኔታ ተካቷል፡፡

ከላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ማፍራትን የፍትሐ-ብሔርተጠያቂነት እንዲኖረው የተመረጠበት ምክንያት ምንጩ ያልታወቀ ንብረት በማናቸውም ሰዎች ላይ ወንጀል ካደረግነው በአሁኑ ወቅት በአገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሕጉ ተጠያቂ ሊያደርጋቸው ከሚችላቸው ሰዎች አንፃር እንዲሁም የማስረዳት ሸክምን ንብረቱን ወደያዘው ሰው አዘዋውረን እንዲህ ዓይነቱን ሰው የምናስር ከሆነ ይህንን ለመሸከም የሚችል በቂ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር በተለይም የማረሚያ ቤትን አቅምን እንዲሁም ለብልሹ አሰራሮች እና የመብት ጥሰቶች ተጋላጭ የሚያደርገው መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ አግባብ ያላስረዳውን እና በህገ-ወጥ መንገድ ያፈራውን ንብረት በመውረስ የፍትሐ-ብሔር ተጠያቂነት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ሲደነገግ "በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ …" የሚለውን በተመለከተ"በቀጥታ" የሚለው በራሱ ስም ያሉ ንብረቶችን የሚያካትት ሲሆን "በተዘዋዋሪ" በሚል የተካተተው ደግሞ በቀጥታ ንብረት በይዞታው ስር ወይም ንብረት በስሙ ሳይኖር ንብረቱን የሚቆጣጠረው (Effective Control) ወይም ተጠቃሚ የሚሆነው ባለቤት (Beneficial Owner) እንዲያካትት በማሰብ ሲሆን ይህንንም ግልጽ ለማድረግ "በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ያፈራው ንብረት" የሚለው ሀረግ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ተብሎ የሚወሰነው ሀብት ግለሰቡ በሕጋዊ መንገድ ካፈራው ንብረት እና ካለው አጠቃላይ ንብረት መካከል ያለው ልዩነት እንደመሆኑ መጠን በምርመራ ወቅት የግለሰቡ አጠቃላይ ንብረት ምን ምን ያካትታል የሚለውን ግልፅ ለማድረግ በምርመራው ወቅት በእጁ የተገኙ ንብረቶችን ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል የተጠቀመው(consumed)፣ያስወገደው(disposed) እና በማናቸውም ሁኔታ ያስተላለፈው(transferred) ንብረቶችንም እንደሚጨምር ተደርጓል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በአንቀጽ 5 ስር ምንጩ ያልታወቀ ንብረት የቅድመ ክስ ሥርዓት እንደ አንድ የመብት መጠበቂያ መንገድ (safeguarding mechanisms) የተካተተ ሲሆን በቅድሚያ የንብረቶቹን ዝርዝር እና የተገኙበትን አግባብ የሚያሳይ መግለጫ ለዐቃቤ ሕግ በማቅረብ ማስረዳት የሚችልበት አግባብ የተቀመጠ ሲሆን ምንጩ ያልታወቀ ንብረት አለው ተብሎ የታመነው ሰው ለዐቃቤ ሕግ ያቀረበው ማስረጃ በቂ ሆኖ ከተገኘ አቃቤ ሕግ ክስ ሳያቀርብ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተለይም የተፈፃሚነት

ወሰኑ በሁሉም ሰዎች ላይ እንደመሆኑ መጠን ሊፈጥረው ከሚችለው የመብት ጥሰት አንፃር ተፈፃሚነቱን በተወሰነ መልኩ መገደቡ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያታዊ የሆነ የወንጀል ጥርጣሬ መኖርን እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ተወስዷል።

በሌላ በኩል በአዋጁ አንቀጽ 6 ስር ምንጩ ያልታወቀ ንብረት የቅድመ ክስ ሥርዓት ተካቷል፡፡ ይህም ሲባል ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ዐቃቤ ሕግ የንብረቱን ዝርዝር እና የተገኘበት አግባብ የሚያሳይ መግለጫ ሕጋዊ የሆኑ ማስረጃዎችን በማቅረብ የሚያስረዳበትን ሁኔታ የሚያስቀምጥ ነው፡፡ የንብረቱን ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው የንብረት ምንጩን ለማስረዳት በራሱ ላይ የወንጀል ኃላፊነት የሚያመጣበት ማስረጃ ቢሰጥም በወንጀል ችሎት ላይ ማስረጃ ሆኖ እንደማይቀርብ በአንቀጽ 7(1) ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ማንኛውም ሰው በራስ ላይ ማስረጃ እንዲያቀርብ ስለማይገደድ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትም ከሌሎች የወንጀልም ይሁን የፍትሐ-ብሔር የማስረዳት ሸክም በተለየ የማስረዳት ሸክሙ በሚጠየቀው ሰው ላይ እንደመሆኑ መጠን በማስረዳት ሂደት በራሱ ላይ የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል ማስረጃ ካቀረበ ይህንን ማስረጃ ብቻ በመጠቀም በወንጀል ተጠያቂ እንዳይደረግ የመብት መጠበቂያ መንገድ (safeguarding mechanisms) ማስቀመጡ አስፈለጊ በመሆኑ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ሆኖም በአንቀጽ 7(3) ስር ዐቃቤ ሕግ በሰጠው ማስረጃ ተመስርቶ በሚያደርገው ምርመራ ሌሎች ማስረጃዎችን ካገኘ እነዚህን ማስረጃዎች በመጠቀም የወንጀል ክስ ከማቅረብ እንደማይከለክል በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ከፈጸመው ወንጀል ነጻ ሊደረግ የማይገባ ከመሆኑም በላይ ከወንጀል ድርጊት መጠቀም ስለሌለበት ዐቃቤ ሕግ የሃብት ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው ካቀረበው ማስረጃ ውጪ ሌሎች ማስረጃዎችን በማደራጀት ወንጀል መፈጸሙን የሚያስረዳ ከሆነ የወንጀል ክሱን ከማቅረብ የሚከለክል ሁኔታ ሊኖር አይገባም፡፡ ሆኖም በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የንብረቱን ምንጭ እንዲያስረዳ የተጠየቀው ሰው ሀሰተኛ ማስረጃ ካቀረበ ሀሰተኛ ሰነድ በማቅረብ በወንጀል ከመጠየቁ ባለፈ ባቀረበው ማስረጃ መሠረት ሌላ የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል ከሆነ ሙሉ በሙሉ በራስ ላይ ማስረጃ እንዳይቀርብበት የተሰጠው መብት ቀሪ ተደርጎ ማስረጃው ጥቅም ላይ ውሎ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በዚህ ሂደትም ይሁን በዋናው ክርክር ወቅት የሚቀርቡ ማስረጃዎች ሕጋዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል በዚህ ጉዳይ መሰረታዊው ጭብጥ የምንጩን ህጋዊነት ማስረዳት እንዳመኑ መጠን ማስረጃዎቹ ተቀባይነት የሚኖራቸው በሕጋዊ

መንገድ የተገኘ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ሀሰተኛ የኦዲት ሪፖርት፣ ሀሰተኛ ዲክራሲዮን ወይም በተለያየ ሁኔታ ሕጋዊ ያልሆነ የሰነድ ማስረጃ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን ለማስረዳት ማቅረብ አይቻልም፡፡ ይህም ሲባል የሚቀርበው ማስረጃ ሕጋዊ መሆን አለበት፡፡ለአብነት ያህልም አንድ ሕጋዊ ንግድ ፍቃድ አውጥቶ የሚሰራ ነጋዴ ወይም ድርጅት ሕጋዊ ገቢው ተብሎ የሚገመተው ለተገቢው ባለስልጣን በወሩ ወይም በአመቱ ከንግዱ ያገኘሁት ብሎ ያሳወቀው የገቢ መጠን ሲሆን ወይም ተገቢው ታክስ የተከፈለባቸው ገቢዎች ሆነው ሲገኙና የታክስ ደረሰኝ ሲቀርብ ሲሆን ከዚህ ውጪ ህጋዊ ታክስ ያልተከፈለባቸው ገቢዎች ከህጋዊ ገቢ ውጪ ያፈራው ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ተብሎ ሊወሰን ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ምንጩን ሲያስረዳ ከውጪ የተላከለኝ ገንዘብ ነው የሚል ግለሰብም ገንዘቡበሕጋዊ መንገድ በባንክ ሥርዓት ውስጥ ያለፉ ግብይቶች ወይም ክፍያዎች ስለመሆናቸው በተገቢው የባንክ ደረሰኝ አስደግፎ ማቅረብ የሚገባው ሲሆን ከዚህ ውጪ ያለው ግን እንደ ምንጩ ያልታወቀ ገቢ ተደርጎ ይቆጠራል ማለት ነው፡፡ ይህን አይነት ሥርዓት በመዘርጋት የአገራችን ኢኮኖሚ በሕጋዊ መስመር ተከትሎ እንዲፈጸም እና ተገቢው ታክስ በአግባቡ እንዲከፈል እና የታክስ ተገዢነት(Tax compliance) እንዲዳብር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበርክታል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 8 ላይ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ክስ የሚቀርብበት ጊዜ እና የገንዘብ መጠን ተደንግጓል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር የተካተተው አዋጁ ወደኋላ 10 ዓመት ተመልሶ የሚሠራ መሆኑንና ይህንንም ለመክሰስ የአምስት ሚሊዮን የገንዘብ ገደብ ተቀምጧል፡፡ ይህም የገንዘብ ገደብ የተቀመጠበት ዋነኛ ምክንያት በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ያለውን የሰው ሃይል፣ የመክሰስ አቅም እና የፋይናንስ አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት አነስተኛ የሃብት መጠን ያላቸውን ግለሰቦች በመተው ከፍተኛ ንብረት ያላቸውን ተጠያቂ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሕጉ ወደኋላ ተመልሶ እንደመስራቱ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ እና የፋይናንስ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርሳሉ ተብሎ የሚገመቱትን ግለሰቦችና ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶችን ተጠያቂ ማድረግ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ስለተገኘ ነው፡፡ በሌላ በኩልአዋጁ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ተጠያቂነት ያለምንም የገንዘብ መጠን ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

### 4.5. <u>ምርመራን በተመለከተ</u>

የንብረት ማስመለስ ሥራ በሌሎች ሕጎች ከተቀመጡት መደበኛ የምርመራ ዘዴዎች በተለየ ሁለት ዓይነት የምርመራ ዘዴዎችን በአንቀጽ 11 ስር እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

እነዚህም የንብረት ማስመለስ የምርመራ ሂደት የተለየ በመሆኑ እንደቅደም ተከተላቸው ጠቅላላ እና ልዩ የምርመራ ዘዴዎችን በመለያየት ይደነግጋል፡፡ በአንቀጽ 10 ጠቅላላ የምርመራ ዘዴዎች ውስጥ ከተካተቱ ዘዴዎች መካከል በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚ እየሆኑና ከእነዚህ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የወንጀል ድርጊቶች እየተስፋፉ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት  የተለያዩ መርመራዎችን ይዟል፡፡ በተለይም የካፒታል ገበያ ሽያጭን በተመለከተ አሁን በአገራችን ውስጥ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ጥቅም ላይ እየዋለ ከመሆኑም በላይ አዲስ ሕግም እየወጣ በመሆኑ በዚህ አዋጅ ይህንን ማካተት ከጊዜው ጋር የተጣጣመ ሕግ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ምናባዊ ንብረት ምርመራ  የክፍያ ስርዓቶች ጋር በተያያዘ በአሁኑ ወቅት የኤሌክትሮኒክ/የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት የተስፋፋ በመሆኑ (ቴሌ ብር፣ኤም ፔሳ እና በተለያዩ ባንኮች የሚደረገውን የዲጅታል የግብይት ሥርዓት) ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የዲጂታል ገንዘብ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚ እንዳይሆን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተከለከለ ቢሆንም አሁን ላይ ወደ ሕጋዊ ስርዓቱ ለማስገባት እና ቁጥጥር ለማድረግ እየተደረጉ ያሉ ጅምር ሂደቶችን ታሳቢ በማድረግ ከጊዜ በኋላ በልዩ ሁኔታ በአገራችን ውስጥ ሊፈቀድ የሚችልበት ሁኔታ የሚያመዝን መሆኑን ግምት ውስጥ ገብቷል፡፡ በተጨማሪም በአለም አቀፍ ደረጃ የዲጅታል ገንዘቦች በተለይም እንደ ቢትኮይን (Bitcoin (BTC))፣ ኤሴሪየም (Ethereum (ETH))፣ ቴዘር (Tether (USDT))፣  ባይናንስ (Binance) ያሉ ዲጅታል ገንዘቦች ወንጀል ፈፃሚዎች ወንጀል ለመፈፀም እና ከወንጀል ፍሬ የሚያገኙትን ንብረት ለማሸሽ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኝ መሳሪያ እየሆነ በመምጣቱ እና ከቅርብ ጊዜያት ወዲህም በሀገራችን ይህን የዲጅታል ገንዘብ አማራጮች የመጠቀም አዝማሚያዎች በመኖራቸው ጉዳዩን ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ የንብረት ምርመራው ወሰን መስፋት እንዳለበት ከግምት ውስጥ በማስገባት ዘመን ተሻጋሪ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የዲጂታል ገንዘብ ጉዳይ በዚህ አዋጅ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

የልዩ ምርመራ ዘዴን በተመለከተ በአንቀጽ 11 ስር የተደነገገ ሲሆን የወንጀል ፍሬንና ከወንጀል ድርጊት የተገናኘ ማናቸውም የንብረት ጥቅም መኖሩን የሚመለከት ማስረጃ ለማግኘት መርማሪው ሲያስረዳና ማስረጃዎቹን መደበኛ ወይም ጠቅላላ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም ማግኘት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ ልዩ የምርመራ ዘዴ ጥቅም ላይ እንደሚውል ተደንግጓል፡፡ የልዩ ምርመራ ዘዴን ከመጠቀም ጋር በተያያዘ በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ በዚሁ ሕግ ላይ ከተቀመጠው ውጪ ልዩ የምርመራ ዘዴ መጠቀም እንደማይቻል በግልጽ የተመለከተ

ቢሆንም ንብረት ማስመለስ ካለው ልዩ ባሕሪ አንጻር የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉን ሙሉ በሙሉ የማይከተል ከመሆኑም በላይ ይህ ሕግ በሚረቀቅበት ወቅት የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ያልጸደቀ በመሆኑና በሥራ ላይ ስላልሆነ ንብረት ማስመለስን በተመለከተ በዚሁ አዋጅ ውስጥ ልዩ የምርመራ ዘዴን መደንገግ ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ ድንጋጌው እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ማስረጃ እንዲቀርብ ወይም እንዲገለጽ የመጠየቅ ሥልጣን ጋር በተያያዘ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚጠየቅ ማንኛውም አካል ወይም ማስረጃው በሚገኝበት ሁኔታ የማቅረብ ወይም የመግለጽ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ "ማስረጃው በሚገኝበት ሁኔታ" ማለትም በጽሑፍ፣ በድምጽ ወይም በምስል ካለ ማስረጃው ባለበት ሁኔታ የማቅረብ ግዴታን የሚጥል ሆኖ ተቀርጿል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መርማሪው ማስረጃው በሚገኝበት ቦታ በመሄድ በጽሑፍ መጠይቅ ማስረጃዎችን የሚሰበስብበት ሁኔታም በአዋጁ ውስጥ ተካቷል፡፡ ማስረጃ ከመጠየቅ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ሰው በይዞታው ስር የሚገኝ ማንኛውንም ማስረጃ በመስጠት የመተባበር ግዴታውን ካልተወጣ የወንጀል ተጠያቂነት በአዋጁ አንቀጽ 52(1) እንደሚያስከትል ተደንግጓል፡፡ የመተባበር ግዴታን በተመለከተ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 24(2) ላይ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 3,000.00 (ሶስት ሺህ ብር) የማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ በጠቅላላው ቢደነገግም ቅጣቱ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚያንስ በመሆኑ ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም እንዲገልጽ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ "በሌሎች አዋጆች የበለጠ ቅጣት የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር" ማስረጃውን እንዲያቀርብ ከመገደዱ በተጨማሪ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እንደሚቀጣ በልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ሥር ስለወንጀል ተጠያቂነት በተደነገገው አንቀጽ ስር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በአንቀጽ 14 ላይ ከማስረጃ ምዘና እና ሥነ-ሥርዓት ከተካተተው ድንጋጌ ጋር በተያያዘ በአዋጁ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም የንብረት ማስመለስ ወይም ውርስ ጉዳይ የሚታየው በፍትሐ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ሲሆን የማስረጃ ምዘናውም በፍትሐ-ብሔር ክርክር የማስረጃ ደረጃ (Preponderance of Evidence) እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ ይህም ማለት የንብረት ማስመለስ ወይም ውርስ የክስ ሂደት በአብዛኛው በፍትሐ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ምዘና እንደሚመራ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ሆኖም በወንጀል ምርመራ ወይም በወንጀል ፍርድ ሂደት የተገኘን

ማስረጃ ለንብረት ማስመለስ ወይም ውርስ በማስረጃነት ሊቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ለዚህም እንደምክንያትነት የሚነሳው በወንጀል ምርመራ ወይም በወንጀል ፍርድ ሂደት የተገኘ ማስረጃ ምዘና ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ (Beyond Reasonable Doubt) የሚያስረዳ ከመሆኑም በላይ አብዛኛውን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች በማክበር የሚሰበሰቡ በመሆናቸው ለፍትሐ-ብሔር የክስ ሂደት ጥቅም ላይ መዋላቸው የሚያስከትለው ጉዳት ስለማይኖር ይህንን ዓይነት ድንጋጌ በዚህ አዋጅ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይህም ሲባል በወንጀል ክርክር ሂደቱ የፍሬ ነገር ክርክሩን በተመለከተ የቀረቡ ማስረጃዎች ላይ በመመስረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በንብረት ማስመለስ ሂደት ይህ ማስረጃ የመጨረሻ ማስረጃ የሚቆጠር መሆኑን በግልጽ በማስቀመጥ በንብረት ማስመለስ ችሎት ማስረጃ እንደአዲስ የማይሰማ መሆኑ በአንቀጽ 14(3) ላይ ተካቷል፡፡

## 4.6. <u>ንብረት ማገድ እና መያዝን በተመለከተ</u>

በአንቀጽ 15(1) ላይ የንብረት ማገድ ወይም መያዝ ማመልከቻ የሚቀርበው የንብረት መውረስ ሊያስከትል የሚችል ምርመራ እየተካሄደ ከሆነ፣ ክስ ከቀረበ፣ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ ወይም ሌላ በቂ የሆነ ምክንያት ሲቀርብ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ላይ "… ሌላ በቂ የሆነ ምክንያት …" በሚል የተካተተው በድንጋጌዎቹ ውስጥ ከተካተቱት ሁኔታዎች በተጨማሪ ሌላ የመከላከል እርምጃዎችን (Preventive Measures) በግልጽ በማካተት ለማለፍ ሲባል ነው፡፡ (ለምሳሌ፡- በካርታ ላይ ካርታ በአንድ ሰው ስም ሲወጣ በሕገ-ወጥ ድርጊቱ የሕጋዊ ሰው መብት ጥሰት እንዳይፈጸም በቅድሚያ ለመከላከል ሲባል ሕገ-ወጥ ካርታ የወጣበትን ንብረት ለመያዝ ማመልከቻ ሊቀርብ ይችላል፡፡)

በመርህ ደረጃ የእግድ ትዕዛዝ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ቢሆንም በልዩ ሁኔታ የሚያዘው ወይም የሚታገደው ንብረት በተፋጠነ ሁኔታ ሊሸሽ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙን ሊያሳጣው የሚችል ድርጊት ስለመኖሩ የሚያሳምን ማስረጃ ያለው እንደሆነ በሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትሩ በሚወክለው ኃላፊ ለሶስት የሥራ ቀናት እንዲታገድ የሚደረግበት አግባብ እና ዝርዝር የአፈጻጸም ሁኔታዎች በአንቀጽ 15(2-5) ላይ ተካቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ሥልጣን ለሚኒስትሩ የተሰጠው በሶስት ቀናት ውስጥ የእግድ ማመልከቻ ለፍርድ ቤት እንደሚያቀርብ በማሰብ ሲሆን ይህንን ጥያቄ ለፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረብ የመዝገብ ቁጥር ማቅረብ በቂ ይሆናል፡፡ ዐቃቤ ሕግ አቤቱታውን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረበ ዕግዱ ቀሪ እንደሚሆን በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ

እግዱ ቀሪ ከመሆኑ በፊት የማገድ ትዕዛዙን የተቀበለው ተቋም ዐቃቤ ሕግ የእግድ አቤቱታ ለፍርድ ቤት ስለማቅረቡ በማረጋገጥ ሊሆን ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ዐቃቤ ሕግ የእግድ ትዕዛዝ በፍርድ ቤት እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ የዕግድ ትዕዛዝ በንብረቱ ላይ እስከሚሰጥ ድረስ በሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትሩ በወከለው ኃላፊ የተላለፈው የእግድ ትዕዛዝ እንደጸና እንደሚቆይ በአንቀጽ 15(4) ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ፍርድ ቤት በታገደው ንብረት ላይ ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ ለመስጠት በቂ ጊዜ እንዲኖረውና በዚህም መካከል የሚፈጠሩ የንብረት መጥፋት እና መወሰር፣ በንብረቱ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ እና እንዳይሸሽ በመከላከል ለፍትሕ ሥርዓቱ ተዓማኒነት ትክክለኛ የሆነ ፍርድ እንዲሰጥ ለፍርድ ቤቱ እድል ለመስጠት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የንብረት መብት በሕገ-መንግሥቱ ጥበቃ የሚደረግለት መብት እንደመሆኑ ንብረት ሲታገድ የማገድ ትዕዛዝ ማመልከቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስራ አምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ መወሰን እንዳለበት በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ የተካተተ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው ፍርድ ቤቱ በንብረቱ ላይ ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ የመስጠት ግዴታ እንደተጣለበት ነው፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ በተለያዩ ምክንያቶች በጊዜ ገደቡ ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ እንደሁኔታው ተጨማሪ የእግድ ትዕዛዝ እንደሚሰጥ በንዑስ አንቀጽ 7 ላይ ተደንግጓል፡፡

ንብረት መያዝን በተመለከተ ንብረት የሚያዘው በተለያዩ ምክንያቶች በእግድ ትዕዛዝ የተፈለገውን ዓላማ ማሳካት ሳይቻል ሲቀር ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለእግድ የሚያደርሱ ሁኔታዎች ተሟልተው የእግድ ትዕዛዝ ብቻ ተገቢውን ዓላማ ሳያሳካ ሲቀርና በአዋጁ አንቀጽ 16(2) ስር ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች መካከል አንዱ ሲሟላ የንብረት መያዝ ማመልከቻ ሊቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ይህም ሲባል በእግድ ትዕዛዝ በንብረቱ ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት መከላከል ወይም ማስቀረት ሳይቻል ሲቀር ንብረቱን መያዝ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ንብረቱ የወንጀል ፍሬ ስለመሆኑ ወይም ለወንጀል መፈጸሚያነት የዋለ ስለመሆኑ ለመጠርጠር የሚያስችል ጠቋሚ ማስረጃ ሲኖር በአዋጁ መግቢያ ላይ በግልጽ እንደተገለጸው ማንኛውም ሰው ከወንጀል ድርጊቱ መጠቀም ስለማይኖርበት ንብረቱን መያዝ ተገቢ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ንብረት እንዲታገድ ወይም እንዲያዝ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚያካትተው የወንጀል

ፍሬን፣ የወንጀል መፈጸሚያን፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን፣ ተመጣጣኝ ንብረት መሆኑን ከግንዛቤ ያስገባ ሃሳብ በአዋጁ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የሥራ ክፍሉ የንብረት ይታገድልኝ አቤቱታ ሲያቀርብ በተጠርጣሪው ወይም በተከሳሹ ስም ከሚገኝ ንብረት በተጨማሪ በትዳር ጓደኛው ወይም ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት የሚኖሩም ከሆነ እና በልጆቹ ስም (የዕድሜ ገደብ ሳይኖረው) የሚገኝ ንብረትም አብሮ እንዲታገድ ሊጠይቅ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 16(3) ላይ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ውስጥ "ሳይጋቡ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ሰዎች" የተካተቱበት ምክንያት በአሁኑ ወቅት ባለው ነባራዊ ሁኔታ አብዛኛውን ጊዜ ንብረት ሳይጋቡ እንደባልና ሚስት በሚኖሩ ሰዎች ስም የሚገኝ በመሆኑ ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሁኔታ ከወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ ሊሆን ስለማይገባ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠር በወንጀል የተገኘ ንብረት በስማቸው ያለ ሳይጋቡ እንደባልና ሚስት በሚኖሩ ሰዎች ስም የተቀመጠ ንብረት በአግባቡ እንዲወረስ በማድረግ በተጨባጭ የሚታዩ ችግሮችን መቅረፍ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ነው፡፡

የእግድ ወይም የመያዝ ማመልከቻ ጋር በተያያዘ በአዋጁ አንቀጽ 17 ላይ የተደነገገ ሲሆን ዐቃቤ ሕግ በአብዛኛው የሚያቀርበው ማመልከቻ ጥቅል በሆነ ንብረት ላይ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የእግድ ትዕዛዝ በሚጠየቅበት ወቅት ንብረት ለመለየት በቂ ጊዜ ስለማይኖር የእግድ ወይም የመያዝ ዓላማ እንዳይስት ወይም ውጤታማነቱን እንዳያጣ ዐቃቤ ሕግ ጥቅል የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ይጠይቅና በቀጣይ የምርመራ ሂደት ተገቢ የሚላቸውን ንብረቶች በአግባቡ በመለየት የወንጀል ፍሬ፣ የወንጀል መፈጸሚያ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት በማስቀረት የቀረውን ንብረት ለባለቤቱ እንዲመልስ በማሰብ ሲሆን ንብረት የታገደበት ሰውም አግባብነት አላቸው የሚላቸውን ማስረጃዎች በማቅረብ ንብረት እንዲለቀቅለት የሚያስችል ሥርዓት በተጓዳኝ ተዘርግቷል፡፡

እግድ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በተመለከተ በአንቀጽ 20 ላይ የተደነገገ ሲሆን በመርህ ደረጃ በንብረቱ ላይ የእግድ ወይም የመያዣ ትዕዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሶስት ዓመት ውስጥ ከንብረቱ ጋር በተያያዘ የተጠረጠረበት የወንጀል ክስ ወይም ንብረቱን የማስወረስ ክስ ካልቀረበ የተሰጠው የመያዝ ወይም የእግድ ትዕዛዝ በሚቀርብለት አቤቱታ መሰረት የአቃቤ ሕግ አስተያየት በማገናዘብ በፍርድ ቤቱ ሊነሳ እንደሚችል የተደነገገ ቢሆንም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል ፍርድ ቤቱ የወንጀሉን ውስብስብነት፣ ድንበር ተሻጋሪ ባህሪ፣ የተጠርጣሪዎችን ብዛትና አቅም፣ የወንጀሉን

ከብደት እንዲሁም ተመሳሳይ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሶስት ዓመት ጊዜውን በቂ ነው ብሎ ለሚያምንበት ጊዜ የማራዘም ፍቅደ ሥልጣን (Discretion) ለፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል፡፡ ይህም ድንጋጌ የተካተተበት ዋነኛው ዓላማ ባለው ነባራዊ ሁኔታ የታገደ ወይም የተያዘ ንብረት ክስ ሳይቀርብበት ለብዙ ዓመታት ታግዶ ወይም ለባለንብረቱ ሳይመለስ የሚቀመጥበት አግባብ በአፈጻጸም ላይ የሚታይ ችግር በመሆኑ እንደየሁኔታው የሚወሰን ሆኖ በመርህ ደረጃ ግን ክስ ሳይመሠረት ለሶስት ዓመት ንብረቱ ታግዶ ወይም ተይዞ ከቆየ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እግዱ የሚነሳበት ወይም የተያዘው ንብረት ለባለቤቱ የሚመለስበት አግባብ እንዲካተት በማድረግ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 40 መሠረት የግለሰቦች መሠረታዊ መብት የሆነው የንብረት መብት የሚጠበቅበት ሥርዓት ተካቷል፡፡

የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ የማይሰጥበት ንብረት ጋር በተያያዘ በአዋጁ አንቀጽ 22 ላይ የተካተተ ሲሆን በፍትሐ-ብሔር ሕጉ የተቀመጡት የእለት መተዳደሪያ ወይም ሙያዊ ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እንዲሁም የቤት ውስጥ መገልገያ የሆኑ ዕቃዎች የተካተቱ ሲሆን በልዩ ሁኔታ እነዚህ ቁሳቁሶች ውድ ከሆኑ ማዕድናት ወይም ከፍተኛ ዋጋ ካለው የእደ ጥበብ ሥራዎች የተሰሩ ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 22(3) መሠረት እንዲታገዱ ወይም እንዲያዙ እንደሚደረግ የተካተተ ሲሆን በምሳሌነትም የወርቅ ማንኪያ ወይም አልጋ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹና በስሩ ለሚተዳደሩ ጥገኞች የሚተዳደሩበት ሌላ ንብረት የሌላቸው ሲሆኑና የሚተዳደሩት ከተያዘው ወይም ከታገደው ንብረት በሚገኝ ገቢ ከሆነ “መሰረታዊ ፍላጎትን ለማሟላት” ይበቃል የሚለውን ያክል ፍርድ ቤት እንደሚወስንና ላልተወሰነ ጊዜ ከታገደው ገቢ ላይ ቀለብ እየተቆረጠለት እንደሚቆይ ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ለእለት ኑሮ የሚሆን የስድስት ወር ስንቅ (ለምግብነት የሚውል) እንዳይታገድ ወይም እንዳይያዝ ያደርጋል፡፡ በአዋጁ ውስጥ ከእግድ ወይም ከመያዝ ነጻ የሆኑ ቁሳቁሶችን፣ የስድስት ወር ስንቅ እና ስለሚቆረጥ ቀለብ ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በአንቀጽ 22(1)(ሀ) ላይ የተቀመጡት የእለት መተዳደሪያ ወይም ሙያዊ ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የእግድ ትዕዛዝ የማይሰጥባቸው ንብረቶች ሲሆኑ በንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ላይ የተካተተው ለእለት ኑሮ የሚሆን የስድስት ወር ስንቅ (ለምግብነት የሚውል) ፍርድ ቤት የእግድ ወይም የመያዝ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት የሚያስቀረው ንብረት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የግለሰቡን የመኖር፣ የቤተሰብ የማስተደዳርና ሰብዓዊ መብት ለመጠበቅ የተካተተ ድንጋጌ ነው፡፡ ሆኖም በአዋጁ

አንቀጽ 22(4) ላይ ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑ በግልጽ ከታወቀ በምንም ዓይነት ሁኔታ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ ከወንጀል ፍሬው የመጠቀም መብት እንደማይኖረው በግልጽ ተካቷል፡፡ ይህም ሁኔታ በቀጥታ የሚያያዘው የአዋጁ ዋነኛ ዓላማ ከሆነው ማንኛውም ሰው ከወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆን እንደሌለበት በተካተተው መርሆ ጋር ነው፡፡

## 4.7. ንብረት መውረስን በተመለከተ

ንብረት መውረስ በጠቅላላው በወንጀል ሕጉ ወይም በሌሎች የወንጀል ድንጋጌዎች የንብረት መውረስ እንደቅጣት ያልተቀመጠ ቢሆንም እንኳን በድርጊቱ ጥቅም መገኘቱ ከተረጋገጠ በዚህ አዋጅ መሠረት ንብረቱ እንደሚወረስ በአንቀጽ 23(2) ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህም ሲባል ማንኛውም ሰው ከወንጀል ድርጊቱ ሊጠቀም የማይገባ ከመሆኑም በላይ በወንጀል ሕጉ መሠረት ንብረት የማይወረስባቸው ነገር ግን በእጅጉ የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስገኙ ወንጀሎች በመኖራቸው ይህንን በአግባቡ በማስረዳት ንብረቱ የሚወረስበትን አግባብ ማካተት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በአንቀጽ 24 ላይ በንብረት መውረስ የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት (Joint and Several liablity) የተደነገገ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ በወንጀል ድርጊት ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች በወንጀል ተግባሩ ለደረሰው ጉዳት ወይም ወንጀሉ ሲፈጸም ለደረሰው ጉዳት ወይም የተገኘው ያልተገባ ጥቅም ለማስመለስ በሚቀርብ የመውረስ ሂደት በመርህ ደረጃ እያንዳንዳቸው ተጠያቂ እንደሚሆኑ በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም በልዩ ሁኔታ (Exeptionally) ከእያንዳንዳቸው ለማስመለስ በቂ ንብረት ለማግኘት ባልተቻለ ጊዜ በአንድነትና በነጠላ እደሚጠየቁ በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ተደንግጓል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በወንጀል ድርጊቱ ኃላፊነት ከተጣለባቸው ተሳትፎአቸው በውል የሚታወቅ ቢሆንም እንኳ ኃላፊነቱንም በእኩል ለመቀበል በማሰብ የሚፈጸም ነው ተብሎ ስለሚገመት የንብረት መውረስን በተመለከተ በአንድነትና በነጠላ እንዲጠየቁ በማድረግ በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በነጠላ ተጠይቆ ክፍያውን የፈጸመው ሰው ቀሪውን ከለሌሎቹ ግለሰቦች በግል ሊጠይቅ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ምክንያቱም ክፍፍሉ በወንጀለኞቹ የግል ግንኙነት የሚወሰን በመሆኑ ይህንን ጉዳይ በራሳቸው መካከል እንዲጠያየቁ ተደርጓል፡፡ በወንጀል ሕጉ መሠረት በወንጀል ድርጊቱ ተጠያቂ ከተደረጉ ከወንጀል ተጠያቂነት ያነሰ የማስረጃ ምዘናን በሚከተለው የንብረት መውረስ ሂደት እኩል ኃላፊነት ሊጣልባቸው ይገባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በአንቀጽ 25(3) ላይ ማንኛውም በወንጀል የተፈረደበት ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የያዘው እና በወንጀል ከመከሰሱ በፊት ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ያፈራው ንብረት ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል ውጤት መሆኑ በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥና ግለሰቡ ንብረቱን በሕጋዊ መንገድ እንዳገኘው ማስረዳት ካልቻለ ንብረቱ የሚወረስበት አግባብ ተደንግጓል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 25(4) ላይ በቅን ልቦና ገዢ ስም የሚገኝ ንብረት ሻጩ የውል ግንኙነቱን የፈጠረው ንብረት ለማሸሽ በማሰብ ከሆነ ይህንን ውል ፍርድ ቤት በማፍረስ የቅን ልቦና ገዢው ለንብረቱ ያወጣውን ገንዘብ ብቻ ተመላሽ በማድረግ ንብረቱ ሊወረስ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህም ምክንያት የቅን ልቦና ገዢው ያወጣውን ወጪና ኪሳራ ከመንግሥት ሳይሆን ከሻጩ እንዲጠይቅ በማድረግ መንግሥት በውሉ ላይ የቅን ልቦና ገዢው የከፈለውን ገንዘብ ብቻ ተመላሽ እንደሚያደርግ ተመልክቷል፡፡

በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስ ሂደትን በተመለከተ ንብረቱ የሚወረስበት ሰው በወንጀል ተከሶ በመጥፋቱ ምክንያት የወንጀል ክሱ ከተቋረጠ ንብረትን በተመለከተ በሚኖረው የክስ ሂደት በወኪል መከራከር እንደማይችል በአንቀጽ 25(5) ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም በዋናነት የተካተተበት ምክንያት ንብረቱ የሚወረስበት ሰው በውክልና የንብረት መውረስ ሂደቱ የሚከራከር ከሆነ ጠፋ ስለማይባል ከመሠረቱ በወንጀል ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስ ሂደትን የሚቃረን በመሆኑ በወንጀል ክሱ ላይ ጠፍቷል ተብሎ ክሱ ከተቋረጠ የንብረት መውረስ ሂደት ያለወኪል የሚታይ ይሆናል፡፡ በሌላ አባባል በወንጀል ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስ ክስ የሚቀርበው ግለሰቡ ጠፍቷል በሚል ስለሆነ ይህ ግለሰብ በንብረት መውረስ ክሱ ላይ በወኪል የሚከራከር ከሆነ ክሱ መቅረብ ስለማይችል በውክልና የሚከራከርበት አግባብ ቀሪ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከተወከለ ግለሰቡን ጠፍቷል ማለት ስለማይቻል በወንጀል ላይ የተመሠረተም ሆነ በወንጀል ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስ ማካሄድ ስለማይቻል መንግሥት ግለሰቡን ቀጥቶ ንብረቱን መውረስ ስለማይችል ይህ ድንጋጌ ተካቷል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 25(7) ላይ ከሕጋዊ ንብረት ጋር ተቀላቅሎ የተገኘ ንብረት የሚወረስበት አግባብ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በመርህ ደረጃ ከሕጋዊ ንብረት ጋር ተቀላቅሎ የተገኘ ንብረት ከወንጀል ድርጊት በተገኘው ንብረት መጠን ልክ የሚወረስ ቢሆንም ንብረቱ በጠቅላላው የሚወረስበት ልዩ ሁኔታም በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ላይ ተካቷል፡፡ ከዚህ አንጻር በወንጀል የተገኘው ንብረት ከሕጋዊ ንብረቱ መጠን ጋር

ተመጣጣኝ ዋጋ ሲኖረው፣ ለሕጋዊ ንብረቱ አይነተኛ ሚና ያለው ሲሆን ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ለንብረቱ ዋና ክፍል ሲሆን ወይም ሕጋዊ ንብረቱን በወንጀል የተገኘው ንብረት ሕጋዊ ለማስመሰል ተጠቅሞት ሕጋዊ ንብረቱ ለወንጀል መፈጸሚያነት ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ተቀላቅሎ የተገኘው ንብረት በጠቅላላው እንደሚወረስ ተደንግጓል፡፡ ተቀላቅሎ የተገኘው ንብረት በጠቅላላው የሚወረስበት ልዩ ሁኔታ በፍርድ ቤት እንደሁኔታው እየታየ እንዲወሰን በማሰብ ለፍርድ ቤት ፍቅደ ሥልጣን ተትቷል፡፡

የንብረት ማስወረስ ማመልከቻ በተመለከተ በመርህ ደረጃ ዐቃቤ ሕግ የንብረት ማስወረስ ማመልከቻ ሲያቀርብ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን እና ሰነዶችን በአግባቡ ፈልጎና አደራጅቶ መሆን እንዳለበት ቢደነገግም በልዩ ሁኔታ ግን ተከሳሹ ንብረት እንዳይገኝ ሆን ብሎ ማስረጃ የደበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ አዲስ የንብረት ማስወረስ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችልና ፍርድ ቤቱም ማመልከቻው ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን ማመልከቻውን እንደሚቀበል በአንቀጽ 26 ላይ ተደንግጓል፡፡ በአጠቃላይ የንብረት ማስወረስ ማመልከቻ የሚቀርበው የወንጀል ፍሬን፣ የወንጀል መፈጸሚያን፣ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትን፣ ተመጣጣኝ ንብረት በመሆኑ የመጀመሪያው ማመልከቻ ሲቀርብ ንብረቱ ሆን ተብሎ ተደብቆ ከሆነ ማንም ሰው ከወንጀል ድርጊቱ መጠቀም ስለሌለበት በልዩ ሁኔታ አዲስ ማመልከቻ በአዲስ ንብረት ላይ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ሆኖም ዐቃቤ ሕግ በተለየ የንብረት መጠን ወይም ዓይነት ያቀረበ እና የተወሰነለት እንደሆነ ግን ንብረቱን በወቅቱ ባያገኝም እንኳ ንብረቱን ባገኘ ጊዜ አዲስ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልገው በአፈጻጸም የተባለውን ንብረት በውሳኔው መሠረት መውረስ የሚችልበትን አግባብ የሚከለክል አይደለም፡፡

ከክስ ነጻ የሚደረግ ምስክርን በተመለከተ በአንቀጽ 27 ላይ ራሱን ችሎ የተደነገገ ሲሆን በወንጀል ምርመራ ሂደት ከክስ ነጻ የሚደረግ እና በወንጀል ክርክር ሂደቱ ወደ ምስክር የዞረ የወንጀል ተካፋይ የሆነ ሰው በወንጀል ድርጊቱ ያገኘውን ንብረት ወይም ያደረሰውን ጉዳት ተመጣጣኝ መጠን ሊከፍል እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡ ማንኛውም ሰው ከፈጸመው ወንጀል ተጠቃሚ መሆን የሌለበት በመሆኑ ከክስ ነጻ የማድረጊያ ስምምነት ሲፈጸም በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ንብረት እንደሚወረስ በግልጽ በማሳወቅ ስምምነቱ ሊፈጸም እንደሚገባ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስምምነቱ ሊፈጸም የሚገባ ቢሆንም የንብረት ውርስ ጉዳይ የድርድሩ አካል ተደርጎ ስምምነት የሚደረግበት

ከሆነም እንደወንጀሉ ሁኔታ እየታየ ንብረት እንዳይወረስ በወንጀል ጥፋተኛነት ድርድሩ ውስጥ እንዲካተትና ንብረቱ እንዳይወረስ ስምምነት ሊደረግ ይችላል፡፡

የንብረት መውረስ በሁለት መንገድ እንደሚፈጸም ከአዋጁ አንቀጽ 29 እና 30 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በጥፋተኝነት ላይ የተመሠረተ የንብረት መውረስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሠረት የንብረት መውረስ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በአንቀጽ 29(2) ላይ ይቅርታ የሚደረገው ከወንጀል ጥፋተኝነት በኋላ ስለሆነ ቅጣቱ በይቅርታ ቀሪ የተደረገለት ማንኛውም ሰው ንብረት የሚወረሰው በጥፋተኝነት ላይ በተመሠረተ የንብረት መውረስ ሂደት እንደሚሆን በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል በአንቀጽ 29(3) ላይ በጥፋተኝነት ላይ የተመሠረተ የንብረት መውረስ ማመልከቻ ሁሉንም የይግባኝ ሂደቶችን አልፎ የመጨረሻ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሚቆጠር ለወንጀል ቅጣት አፈጻጸም በወንጀል ሕግ በተቀመጠው የይርጋ የጊዜ ገደብ ውስጥ ዐቃቤ ሕግ ማመልከቻውን ማቅረብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይህም ማለት በጥፋተኝነት ላይ የተመሠረተ የንብረት መውረስ እንደወንጀል ቅጣት አፈጻጸም ተቆጥሮ የወንጀል ሕጉ ለቅጣት አፈጻጸም የሚያስቀምጠው የይርጋ ጊዜ እንደወንጀሉ አይነት ተፈጻሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በአንቀጽ 30 ላይ የተደነገገው በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስን በተመለከተሲሆን በመርህ ደረጃ ንብረት የሚወረሰው በወንጀል ጥፋተኝነት ላይ ተመስርቶ ቢሆንም በተለየ ሁኔታ በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስ ሁኔታዎች እንዳሉ በግልጽ ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡ አዋጁ በተለየ ሁኔታ ዘርዝሮ ያስቀመጣቸው የማስወረሻ ምክንያቶች በዋናነት የወንጀል ጉዳዩ የጥፋተኛነት ውሳኔ ማስጠት የማይቻልባቸው በመሆናቸው ነው፡፡ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሳይሰጥ የሚቀርብ የውርስ ጥያቄ መሰረቱ እንዲወረስ የሚጠየቀው ንብረት ከወንጀል ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ ነው፡፡ ምንም እንኳን የወንጀል ጥፋተኛነት ባይሰጥም በወንጀል ምክንያት የተገኘ የንብረት ጥቅም እንዳለ ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን ከጠቅላላ መርሁ አንጻር ማንም ሰው በወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በአንቀጽ 30(2)(ሀ) እስከ (ቀ) የተቀመጠው የወንጀል ጉዳዩን የሚመራው ሥነ-ሥርዓት ሂደት እና በሌሎች ምክንያቶች የወንጀሉን ተጠያቂነት ማስቀጠል የማይቻል ከሆነ ወይም የሚቋረጥበት ሁኔታ ሲፈጠር ወይም በማንኛውም ምክንያት የወንጀል ጥፋተኛነት ውሳኔ ማሰጠት የማይቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ እና ከወንጀል የተገኘ ጥቅም መኖሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ መውረስ እንዲቻል የተቀመጠ ነው፡፡

## 4.8. ንብረት ማስተዳደርን በተመለከተ

በአዋጁ ንብረት እንዳይበላሽ፣ እንዳይጠፋ፣ ዋጋው እንዳይቀንስ ወይም ባለበት እንዲቆይ እና በአጠቃላይ የሚወረስ ነገር እንዳይጠፋ የንብረት አስተዳደርን ሥርዓት የሚመሩ ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በቅድምያ የተያዘውን ወይም የታገደውን ንብረት በሚመለከት ኃላፊነት የሚወስድ ሰው እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የንብረት አስተዳዳሪ የሚሾምበትን ሁኔታ በአንቀጽ 31 እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይህን በተመለከተ ሂደቱ በመርህ ደረጃ በፍርድ ቤት እንዲሾም እና ሲሾምም የዐቃቤ ሕግን እና የንብረት ባለመብቱን አስተያየት መስማት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን የንብረት ባለቤት ሊገኙ ሳይችሉ ሲቀር ወይም ለመቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆኑ የንብረት አስተዳዳሪ የመሾም ሁኔታ እንዳይደናቀፍ የንብረት ባለቤቶች በአማራጭ እንዲሰሙ ማለትም የንብረት ባለቤቱን ማግኘት ሲቻልና በፈቃደኝነት ሲቀርብ ብቻ አስተያየት እንዲሰጥ በአንቀጽ 32(3) ላይ በመደንገግ ታልፏል፡፡

ንብረት ማስተዳደርን በተመለከተ ዐቃቤ ሕግ የሚኖረውን ኃላፊነት በአንቀጽ 36 ላይ የተደነገገ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይም ዐቃቤ ሕግ የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠበትን ንብረት እንደሚቆጣጠር ተደንግጓል፡፡ ይህም የተካተተበት ምክንያት ዐቃቤ ሕግ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበት ንብረት ላይ መደበኛ ቁጥጥር በማድረግ ንብረቱ ያለበትን ሁኔታ በመገምገም ንብረቱ አላግባብ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን፣ ንብረቱን ለማጥፋት እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ካረጋገጠ ንብረቱ ሊያዝ ስለሚገባ ይህንኑን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ንብረቱ እንዲያዝ ማድረግ ስለሚገባ ዐቃቤ ሕግ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ንብረትም ላይ መደበኛ ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

## 4.9. የተወረሰ ንብረት አጠቃቀም በተመለከተ

በዚህ አዋጅ መሠረት ከተወረሰ ጥሬ ገንዘብ ወይም ንብረት ሽያጭ የሚገኝ ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ሂሳብ እንደሚከፈት በአንቀጽ 37(1) ላይ ተደንግጓል፡፡ ይህም የተደረገው በዋናነት በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተደነገገው የሚወረስ ንብረት ጋር በተያያዘ ጉዳት የደረሰበት ተጎጂ ሲኖር ለደረሰው ጉዳት ትክክለኛ ዋጋ ታስቦ ካሳ እንዲከፈል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የንብረት ማስመለስ ሥራ ልዩ የምርመራ ዘዴዎችን የሚከተል ከመሆኑም በላይ የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶችን ስለሚያጠቃልል በሚኒስቴሩ ለሚሠሩ የፍትሕ አስተዳደር ሥራዎች

የአቅም ግንባታ እና በንብረት ማስመለስ ሥራ ሊውል እንደሚችል በማሰብ ነው፡፡ የፍትህ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ለሚሳተፉ አካላት ማጠናከሪያ የሚውለው ገንዘብ አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እንደሚወሰን በግልጽ ተመላክቷል፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ ጥቅም ላይ የሚውለው ንብረት የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ እና በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ መሠረት የተቋቋመው የተጎጂዎች ፈንድን የሚነካ እንዳልሆነ በአዋጁ አንቀጽ 37(6) ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

### 4.10. <u>ዓለም አቀፍ ትብብርን በተመለከተ</u>

በሕግ ጉዳዮች ዓለም-አቀፍ ትብብርን በተመለከተ በወንጀል-ሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕጉ ላይ የተካተተ ቢሆንም ከንብረት ማስመለስ ጋር በተያያዘ የተካተቱ ድንጋጌዎች በቂ ባለመሆናቸው (ሁለት ድንጋጌዎች ብቻ ናቸው) ንብረት ማስመለስ ጉዳይን በተመለከተ የዓለም-አቀፍ ትብብር በዚህ አዋጅ ውስጥ እንዲካተት ራሱን ችሎ በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲደነገግ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሕግ የጋራ ድጋፍ ትብብር ወጪን በተመለከተ በአንቀጽ 45 ስር የተካተተ ሲሆን መደበኛ የምርመራ ወጪ የተለመደ በመሆኑ በኢትዮጵያ የሚሸፈን ሲሆን ከተለመደው መደበኛ የምርመራ ወጪ በላይ የሆነ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ከሆነ ከጠያቂው ሀገር ጋር በሚደረግ የሁለትዮሽ ስምምነት እንደሚወሰን ተደንግጓል፡፡

### 4.11. ለጠቋሚዎች የሚሰጥ ማበረታቻ

በአዋጁ ላይ  ከተካተቱ ሃሳቦች መካከል አንዱ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ላይ ጥቆማ ለሚያቀርቡ ሰዎች ስለሚሰጥ የጠቋሚዎች ማበረታቻ የተደነገገው (Reward Act) ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚመለስና የሚወረስ ንብረትን በተመለከተ ጥቆማ ቀርቦ በተሰጠው ጥቆማ መሠረት ንብረቱ የተወረሰ እንደሆነ የጠቋሚ ማበረታቻ ክፍያ እንደሚከፈለው ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን ጥቆማውን ያቀረበው ሰው በማንኛውም ሁኔታ በሙያው አማካኝነት መረጃውን ያገኘ ሰው ሊሆን አይገባም፡፡ ይህም ሲባል ከምርመራ ሥራው ወይም ከክስ ሂደት ጋር በተያያዘ መረጃውን ሊያውቅ የሚችል ማንኛውም በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሚሠራ ሰውን የሚያካትት አይሆንም፡፡ ይህም ሲባል በማንኛውም ሁኔታ ከምርመራ ሥራው ወይም ከክስ ሂደት ጋር በተያያዘ መረጃውን ከሚያውቅ ሰው ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ያለው ሰው አሳልፎ የሰጠው መረጃ ከሆነ የጠቋሚ አበል እንደማይከፈለው በግልጽ በንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ ተደንግጓል፡፡

## 4.12. የሥራ ክፍል ስለማደራጀት

በዚህ አዋጅ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ውስት ከተካተቱ ድንጋጌዎች መካከል የሥራ ክፍል የሚደራጅበት አግባብ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የንብረት ማስመለስ ሥራን የሚሠራ የሥራ ክፍል በሚኒስቴሩ እንደሚደራጅ በአንቀጽ 49(1) ላይ በግልጽ ተመልክቷል። ይህ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተተው በአዋጅ ቁጥር 1263 መሰረት ፍትህ ሚኒስቴር የንብረት ማስመለስ ስራ እንዲሰራ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፥ ይህንን ስልጣኑን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የስራ ክፍል ማደራጀት እንዳለበት ግልፅ ለማድረግ ታስቦ ነው። ይህ ልምድ በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት ውስጥ የሚታወቅ ሲሆን ለምሳሌ በመንግሥትና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010 ላይ የሥራ ክፍል (ዳይሬክቶሬት ጀነራል) በአዋጅ የተቋቋመበትን ሁኔታ አለ፥ እንዲሁም በግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649 ላይም ተመሳሳይ ድንጋጌዎችን እናገኛለን። ከዚህ አንጻር የንብረት ማስመለስ ሥራ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን የያዘና ከብዙ ወንጀሎች ጋር የተቆራኘ እንደመሆኑ ሥራውን በአግባቡ ለመሥራትና በተጨባጭ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ ውጤታማ የሆነ የንብረት ማስመለስ ሥራ እንዲከናወን በአንድ ማዕከላዊ በሆነ አደራጀጀት ውስጥ ራሱን የቻለ ዐቃቤ ሕግ፣ መርማሪ እና ልዩ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎችን ማለትም ኦዲተር፣ ንብረት ገማች (Asset Evaluator)፣ የሂሳብ ባለሙያዎች (Accountants) ወይም ኢንጅነሮች የሚያስፈልጉት በመሆኑ በዚህ መልኩ የተዋቀረ የሰው ኃይል አደረጃጀት ኖሮት በፍትሕ ሚኒስቴር ስር እንዲደራጅ የተደረገ ሲሆን የሚኖረው የአሠራር ሥርዓት በተቋሙ ውስጣዊ መዋቅር የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 4.13. የዳኝነት ሥልጣንን በተመለከተ

የዳኝነት ሥልጣንን በተመለከተ በልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ስር በአንቀጽ 51 ላይ የተደነገገ ሲሆን በዚህም መሠረት ፍሬ ነገሩን የሚያየው ፍርድ ቤት የንብረት መውረስ ጉዳዮችንም እንዲያይ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በጥፋተኝነት ላይ የተመሠረተ የንብረት መውረስ የወንጀል ድርጊቱን የመዳኘት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት እንደሚያየው የተደነገገ ሲሆን በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስ ሲሆን ደግሞ የወንጀል ክስ ቢቀርብ ኖሮ ፍሬ ነገሩን ያየው የነበረው ፍርድ ቤት የመዳኘት ሥልጣን እንደሚኖረው በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን በሚመለከት በጉዳዩ ውስጥ ያለውን የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች በሚዳኝበት አግባብ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ምንም

እንኳን በወንጀል የሚጠረጠሩ ሰዎችን የሚመለከት ቢሆንም የስረ-ነገሩ ኃላፊነት እንዲሁ እና ሂደት በአብዛኛው የፍትሐ ብሔር ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡

## 4.14. የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ

በአዋጁ አንቀጽ 52(2) ላይ ማስረጃ የተጠየቀው ሰው ማስረጃን የደበቀ ከሆነ፣ ሃሰተኛ ማስረጃ የሰጠ ከሆነ ማስረጃውን ያጠፋ ከሆነ መረጃ መጠየቁን ሚስጢራዊነት ያልጠበቀ ከሆነ "በሌሎች አዋጆች የበለጠ ቅጣት የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር" በዚህ አዋጅ ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነትን በተለይም በሙስና ወንጀሎች አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ ላይ የተቀመጡ ተመሳሳይ ወንጀል ድንጋጌዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከእነዚህ ሕጎች ውጪ ያሉ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ተጠያቂ የሚሆኑበት አግባብ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

በወንጀል ድርጊት የተገኙ ንብረቶችን የማስመለስ ሂደት በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተበታትኖ የሚገኝ በመሆኑ የንብረት ማስመለስ እና ማስተዳደር አዋጅን በማዘጋጀት የንብረት ማስመለስና መውረስ ሁኔታ በተለይም በጥፋተኝነት ላይ የተመሠረተ እና በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሠረተ የንብረት መውረስ ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችን ያካተተ ወጥ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፡፡

ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ጋር በተያያዘበአሁኑ ወቅት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ለመንግሥት እና ለህዝባዊ ድርጅት ሠራተኞች ብቻ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ ከመንግሥት እና ከህዝባዊ ድርጅት ሠራተኞች ውጪ ያሉ ግለሰቦችንና ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች ምንጩ ባልታወቀ ንብረት በፍትሐ-ብሔር የሚጠየቁበትን አግባብ ያካተተ ሕግ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህም በመርህ ደረጃ ምንጩ ያልታወቀ ንብረት የሚወረሰው ምክንያታዊ የወንጀል ጥርጣሬ ሲኖር የሚነሳ ጉዳይ መሆኑን በግልጽ የሚያካትት ድንጌዎችን እንዲይዝ ተደርጎ ተቀርጿል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከንብረት ማስመለስ ጋር በተያያዘ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ንብረት በሚመለከት ጥቆማ የሚያቀርብ ሰው የሚሸለምበት (Reward Act) አዲስ ሥርዓትም ተዘርግቷል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ አዋጅ ከተለያዩ የወንጀሎች ድርጊቶች የሚመነጩ ንብረቶችን በአግባቡ ወጥ በሆነና በተደራጀ መልኩ የሚሠራበትን የሕግ

ማዕቀፍ ከመቅረጽ ባለፈ በፍትሕ ሚኒስቴር ስር በሚደራጅና በአዋጁ እውቅና የተሰጠው ራሱን የቻለ የሥራ ክፍል በማደራጀት ውጤታማ የሆነ የንብረት ማስመለስ ሂደት ተግባራዊ የሚደረግበት ሥርዓት መዘርጋትን ያካትታል፡፡